ዲሞክራሲያችን “Made in …” ይለጠፍበት!

እኔ የምለው … የምርጫ ህጋችንን ከየት አገር ነው የኮረጅነው? (ኩረጃ ማሳፈሩ ተረት ሆኗል ብዬ ነው) ለምሳሌ … የፀረ ሽብር ህጉ ከየት ነው የተኮረጀው? የምርጫ ስነ ምግባር ኮዱስ? የሲቪክ ማህበረሰባትና የመያዶች አዲሱ አዋጅስ? ሁሉም እኮ በዲሞክራሲ የዳበረ ልምድ አላቸው ከተባሉ አገራት ቃል በቃል የቀዳውት ነው የሚለን (መቼም ከቻይና አይቀዳ!) ይልቁንስ ምን እንደሚያስፈራኝ ልንገራችሁ … አብዛኞቹን ነገሮች ከዚህም ከዚያም እየኮረጅን አይደል! በተለይ ህግና መመሪያዎችን ከየአገራቱ ኢምፖርት አድርገን እዚህ እኮ ነው የምንገጣጥመው (እንደ መኪና!) ለነገሩ ኢህአዴግ ጨዋ ስለሆነ መኮረጁን ነግሮን ነው እንጂ “Made in …” የሚል እኮ አይለጠፍበትም፡፡ ምን ሃሳብ እንደመጣልኝ ታውቃላችሁ (የተኮረጀ ግን አይደለም!) የአገራችን ዲሞክራሲ የተመረተበት አገር (Made in…) ቢለጠፍበት ጥሩ አይመስላችሁም? (የቻይናን ከአሜሪካው ለመለየት ብዬ እኮ ነው!) ያው የቻይና ዲሞክራሲ እንደ አንዳንድ ምርቶቿ ፌክ እኮ ነው፡፡ ትዝ ይላችኋል… ሴቶቻችንን ከቦይፍሬንዶቻቸው ሊያቀያይሟቸው የደረሰ የቻይና ጫማ መጥቶ ነበር እኮ (የሚያቃጥል!) የቻይና ዲሞክራሲ እንደዚያ ጫማ ነው (ፌክ!) ብቻ ሁሉ ነገር የተመረተበት አገር ስም ቢኖርበት ከመሸወድና ከመክሰር እንድን ነበር፡፡ እኔ የምለው… ገዢው ፓርቲ ለ21 ዓመታት የሙጥኝ ያለው “አብዮታዊ ዲሞክራሲ” ርእዮተ ዓለም አገሩ የት ነው? (ብቻ ከቻይና እንዳይሆን!) እርግጠኛ ነኝ አንድ ቀን ራሱ ኢህአዴግ የኮረጀበትን አገር ራሱ ይናዘዝልናል፡፡ የምርጫ (Election) ስታይላችንም የተመረተበት አገር ቢታወቅ ከብዙ ንትርክ ያድነን ነበር፡፡ ለምሳሌ… የ”ምርጫ” ስታይላችንን ኢምፖርት ያደረግነው ከቻይና ነው ከተባልን አርፈን እንቀመጣለን፡፡ (ፎርጅድ ናታ!) አያችሁ …ሰሞኑን 34 ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከምርጫ ቦርድ ጋር ውዝግብ ውስጥ የገቡበት ምክንያት የምርጫ ስታይላችን ከየትኛው አገር ኢምፖርት እንደተደረገ (በኢህአዴግ ቋንቋ እንደተቀዳ) ባለማወቃቸው ነው፡፡ እስቲ አስቡት… የምርጫ ስርዓቱ “Made in China” ነው ቢባሉ በምርጫ ቦርድ ላይ ያላቸውን የገለልተኝነት ጥያቄ ሁሉ እርግፍ አድርገው ይተውት ነበር:: (የቻይና ምን ሊጠቅም!)